የሰበር መ/ቁ. 32545

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ሽፈራው ጠበቃ ባዩ ደስታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የክርስቲያን በጎ አድራጎት ልማት ድርጅት ጠበቃ አድማሱ መዓዛ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቂራ ምድብ የሥራ ክርክር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 22417 ሚያዚያ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰኔ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ አመልካች ተጠሪው ብር 19173.70 /አስራ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ ሰባ ሶስት ብር ከሰባ ሣንቲም/ ፕሮቬደንት ፈንድ እንዲከፍላቸው ያቀረቡት ክስ ተጠሪው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ያቀረበውን ክርክር በመቀበል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩ በይርጋ ቀሪ ይሆናል ብሎ ውሣኔ በመስጠቱና የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይህንኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ በማጽደቁ ነው፡፡

አመልካች ፕሮቪደንት ፈንድ ከሠራተኛው ደመወዝ በየወሩ በፐርሰንት እየተቀነሰ በአሰሪው የሚቀመጥና የሚጠራቀም ሠራተኛው ከሥራ ሲሰናበት የሚጠቀምበት በጡረታ መልክ የሚከማች የሠራተኛው ገንዘብ ነው፡፡ ይህ



ገንዘብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2800 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2802 የተቀመጠ በመሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1756 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ባለመብቱ ሲጠይቅ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል ስለሆነ በይርጋ ይቋረጣል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪው በበኩሉ፤ ፕሮቪደንት ፈንድ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ያለውን ትርጓሜ በመጥቀስና ፕሮቪደንት ፈንድ የሰራተኛ ጥቅማጥቅም በሚባሉት ውስጥ፤ የሚመደብ እንደሆነ በመግለጽ እንደዚሁም ፕሮቪደንት ፈንድ ሠራተኛው 5% አሠሪው ደግሞ 15% በማዋጣት በባንክ በተከፈተ ሒሣብ እንደሚቀመጥ በመግለጽ፣በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይና በሰበር በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ከሥራ ቅጥር ውል የሚመነጩ የደመወዝ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ጥያቄዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መቅረብ ያለባቸው መሆኑን በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ክፍያዎች በመሰረታዊነት ሰራተኛው ስራ ላይ እያለ የይገባኛል ጥያቄ ሊያቀርብ እና የመብት ጥያቄ ሊነሣ የሚችልባቸው ናቸው፡፡

ይህ ከሆነ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ፣ በባህሪው ከደመዝ ጭማሪ፣ ከትርፍ ሰዓት እና በዓል ቀን ክፍያ የተለየ ነው፡፡ የገንዘቡም ምንጭ ቢሆን ሙሉ በሙሉ አሠሪው አይደለም፡፡ ከተጠራቀመው ገንዘብ ውስጥ፣ከሠራተኛው በየወሩ አምስት ፐርሰንት እየተቆረጠ ተቀምጧል፡፡ ዓላማውም ሠራተኛው ከሥራ ሲሰናበቱ ወይም ሥራውን በራሣቸው ፈቃድ ሲለቁ፤ እነሡና ቤተሰቦቻቸው ችግር ላይ እንዳይወድቁ፣ ለመደጎምና የማህበራዊ ደህንነትና ዋስትና ክፍያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ፕሮቪደንት ፈንድ ይከፈለኝ የሚለው ጥያቄ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/1996 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ገንዘቡ የአደራ ገንዘብ በመሆኑ በተጠየቀ በማናቸውም ጊዜ ሊከፈል ይገባዋል በማለት ያቀረበው ክርክር ፕሮቪደንት ፈንድ ባለባቸው መሥሪያ ቤቶች የሚተዳደሩ ሠራተኞች በሕይወት ባሉበት በማናቸውም ጊዜ ወይም የእነርሱ ወራሾች፤ መብቱን ሊጠይቁ ከሚችሉበት ቀን አንስቶ፣ ከሃያ ዓመት በኋላ፣ ከሃምሣ ዓመት በኋላ እና ከዚያም በላይ እየመጡ፣ ጥያቄ እንዲያቀርቡ እድል የሚሰጥ ነው፡፡ ይኸ ደግሞ የሚበረታታና የሕግ ጥበቃ የሚሰጠው አይደለም፡፡ ስለሆነም ፕሮቪደንት ፈንድ፤ በስንት ዓመት ውስጥ መጠየቅ እንደሚገባው የሚደነግግ ግልጽ የሕግ ድንጋጌ ባይኖርም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1677 አንቀጽ 1 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 መሠረት መታየት ያለበት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ፕሮቪደንት ፈንድ ባለመብቱ በአስር ዓመት ውስጥ ካልጠየቀ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለው የሥራ ውል የተቋረጠው ጥቅምት 29 ቀን 1992 ዓ.ም በመሆኑ፣ ፕሮቪደንት ፈንዱን ተጠሪ እንዲከፍለው ያቀረበው ጥያቄ አስር ዓመት አልሞላውም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀራ ምድብ ችሎት አመልካችና ተጠሪ የሚያደርጉትን ሌሎች የፍሬ ጉዳይና የሕግ ክርክር በመስማትና ማስረጃቸውን በማመዛዘን የመሰለውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡



3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሣቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት